# ስለ ወ/ት ብርቱካን ጠቅላይ ምኒስትር መለስ የማይደፍሩት ሀቅ፤

ሰላማዊት

ጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ በአሜሪከው ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ተገኝተው ስለ ወ/ት ብርቱከን ሚደቅሳ ሲጠየቁ በየመድረኩ ከሚለዋውጡት ምላሽ አንዱን መለሱ፡፡« ይቅርታ አልጠየኩም የሚል ሰው በህጋችን መሰረት ይቅርታው ተነስቶ ውሳኔው ተፈጻሚ ይሆናል አሉ» ፡ (ቃል በቃል ስለመጥቀሴ ርግጠኛ አይደለሁም፡፡ የትኛው ህግ ይህን እንደሚል ግን አንቀጽ ጠቅሰው ማስረዳት አይችሉም፡፡ እንዲህ የሚል ደንጋጌ የያዘ አዋጅም ሆነ ደንብ የለም፡፡

ጠቅላይ ምኒስትሩ ብርቱከን ከታሰረችበት ጊዜ አንስቶ ስለ ጉዳዩ መጠየቃቸው አልቀረም፡፡ ምላሻቸው ግን አንድም ግዜ ተዛምዶ አያውቅም ሀሙስ መጋቢት 9/2002 በየተራ ለሀገር ውስጥና ለውጪ ጋዜጠኞች መግለጫ በሰጡበት ወቅት የተናገሩትን ብንመልከት ሰሞኑን ከተናገሩት ፈጽሞ አይዛመድም፡፡

ከሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች ጋር በነበራቸው ቆይታ አንድ ‹ልማታዊ ›የሚመስል ጋዜጠኛ ሰብአዊ መብት ጣሳችሁ እየተባለ ጩኸት የሚበዛው ለምንድን ነው ሲል ጠየቀ፡፡ አቶ መለስ ሲመልሱ ችግሩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞ ሳይሆን መንግስታቸው የሚወስዳቸው አንዳንድ ርምጃዎች የሚያስኮርፋቸው የውጪ ኂያሎች የሚያቀነባበሩት ሴራ እንደሆነ ገለጹና ለምሳሌ ብለውም የሲቪክ ማህበራት አዋጁንና የወ/ት ብርቱካንን እስር አነሱ፡፡ ጥያቄው የፓዎር ጉዳይ ነው፡፡ የማን ህግ የበላይ ነው የሚል ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን የታሰሩት መግለጫ ስጡ ተብለው እንቢ ስላሉ ነው አሉ ጠቅላይ ምኒስትሩ፡፡ የወ/ት ባለፈው ሁለት ዓመት የወ/ት ብርቱካንን እስር አስመልክቱ አቶ መለስን ጨምሮ ይመለከተናል ብለው መግለጫም ሆነ ማብራሪያ ለመስጠት የሞከሩ ሁሉ የአንዳቸው ከአንዳቸው ቃል አይዛመድም፡፡ በተለያየ ቀን የሚናገሩትም ርስ በርስ የሚጣረስ ነው፡፡ ጥቂት ምሳሌ ከጠቅላይ ምኒስትሩ የተለያየ ግዜ ንግግር ማሳየት ይቻላል፡፡

የካቲት 7/2001 ዓም የተነበበው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ‹ጠቅላይ ምኒስትሩ በይቅርታ ሕግ ጉዳይ ለቀረበላቸው ጥያቄም መንግስት ይቅርታ ከጠየቁ ግለሰቦች ጋር ምንም አይነት የሽምግልና ጉዳይ እንዳላካሄደ አመልክተው…..› ይላል፡፡ በዛው ሰሞን ከቢቢሲዋ ጋዜጠኛ ዘይነብ በደዊ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ደግሞ ‹ይቅርታ የተሰጣቸው በሀሰተኛ ግምት ነበር፤እናም በህጋችን መሰረት ማንኛውም በሀሰተኛ ግምት የተሰጠ ይቅርታ በአፋጣኝ ውድቅ ሊሆን ይገባል ›አሉ፡፡ ይሄው አሁን ደግሞ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ሄደው ወ/ት ብርቱካን ለእስር የበቁት ይቅርታ አልጠየኩም ስላሉ ነው አሉ፡፡ አቶ መለስ በአለፈው ሁለት ዓመት ስለ ብርቱካን እስር የተናገሩትን ወደ ኂላ ሄደን ብንፈትሽ እንዚህን መሰል ፈጽሞ የማይገናኙ ብዙ ማግኘት እንችላለን፡፡ይህ በራሱ ታዲያ ወ/ት ብርቱካን ለምን በማንና በምን ምክንያት ነው የታሰሩት የሚል ጥያቄ ለማንሳት በቂ ይሆናል፡፡

በድፍረታቸው የሚታወቁት አቶ መለስ የማይናገሩት፤ጋዜጠኞች ሊያነሱት ያልሞከሩት፤ፖለቲ ከኛ ተብዬዎቹ ፈንጂ የመርገጥ ያህል የሚሸሹት አንድ የህሊናቸው ጌታ የሆኑ ዜጋ ብቻ ደፍረው የጻፉበት የወ/ት ብርቱካን እስር ምክንያቱ ይቅርታው የተከናወነው በሽምግልና መሆኑን የመንግስት ባለሥልጣኖች ማመን አለመፈለጋቸው ነው፡፡

የአቶ መለስን የቅርቡን ንግግራቸውን ይቅርታ አልጠየኩም በማለታቸው ነው የታሰሩት ያሉትን ብቻ ይዘን ይህን ጭብጥ የሚያስረዳ ክርክር እንዳርግ፡፡ የይቅርታን ምንነት እንዲት በማንና መቼ ተፈጻሚ እንደሚሆን ብሎም በምን ምክንያት ስለምንና በማን ይቅርታ ሊነሳ እንደሚችል ለዚሁ ተብሎ ተለይቶ የወጣው የይቅርታ ስነ-ሥርኣት አዋጅ 395/96 በሚገባ ይዘረዝራል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4(3) በፕሬዝዳንቱ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ የሚሰጣቸው ሰዎች ቅድመ ሁኔታውን አላሟሉም ወይንም ጥሰዋል የሚል ክስ ሲቀርብባቸው ጉዳዩን መርምሮ ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል ›በማለት ግልጽ ስልጣን የሰጠው ለይቅርታ ቦርዱ ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን ግን የተጠሩት ወደ ፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ሲሆን ያነጋገሩዋቸውም ያስፈራሩዋቸውና ማስጠንቀቂያ የሰጧቸው ማለቱ ሳይሻል አይቀርም ሁለት የፖሊስ ባላሥልጣናት ናቸው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም የአዋጁ አንቀጽ17(1) ይቅርታ ለማሰረዝ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ከተገኘ ምክንያቱ በግልጽና ይቅ ርታ የተደረገለት ሰው በሚገባው ቋንቋ

በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለይቅር ተባዩ እንዲደርሰው ይደረጋል › ሲል 17( 2) ደግሞ ይቅር ተባዩም ጽሁፉ በደረሰው ቢበዛ በሀያ ቀናት ውስጥ መልሱን ማቅረብ ይኖርበታል፡ በማለት ይገልጻል፡፡

ክቡር ጠቅላ ምኒስትር ወ/ት ብርቱካን ይቅርታ አልጠየኩም ስላሉ ነው መልሰው የታሰሩት ሲሉ በህጋችን ያሉት የትኛው ህግ እንደሆነ አላስረዱም፡፡ ከአፈርኩ አይመልስን አይነት ለአንድ ጉዳይ የተለያየ ምክንያት እየሰጡ ቀጠሉ እንጂ የተፈጸመውን ድርጊት ከሕጉ ጋር አገናዝበው አልተመለከቱም ወይንም በወቅቱ ስቀላት ስቀላት ሲሉ የነበሩት በዙ ሪያቸው የነበሩ አንዳንዶቹ የሚሉዋቸውን ብቻ እየሰሙ በስህተቱ መንገድ መቀጠሉን መርጠዋል፡፡ ሆኖም ግን ዛሬም ከሁለት ዓመት በኋላ መለስ ብሎ ማየት ከተቻለና ከአፈርኩ አይመልሰኝ እንደማይጠቅም መገንዘብ ከተቻለ ማረም ይቻላል፡፡

አስቲ ቀላል ግን መሰረታዊ ጥያቄዎችን እናንሳ፡፡ ወ/ት ብርቱካን ይቅርታ ኢጠየኩም ብለዋል ከተባለ ህጉን ተከትሎ ለምን ቦርዱ አልጠየቃቸውም፤ለምንስ በጽሁፍ አልገለጸላቸውም፡፡ የፖሊስ ባለሥልጣናት በምን የህግ አግባብ ነው ጠያቂና በመንግስት መገናኛ ብዙሀን አማካኝነት ሶስት ቀን ሰጥተናታል እያሉ አስፈራሪ የሆኑት፡፡ በዛ ህገ ወጥ አካሄድ ወ/ት ብርቱካን የት ማን ዘንድ ምንስ ብለው መግለጫ እንዲሰጡ ነበር የተፈለገው፡፡ በመገናኛ ብዙሀን ለተነገራቸው በሚያስተናግዳቸው መገናኛ ብዙሀን አማካኝነት የሰጡት መልስ ሊታይ ያልቻለውስ ለምንድን ነው፤ቦርዱ በህግ አግባብ ባላጣራው ጉዳይ ላይስ ፕሬዝዳንቱ ወስነዋል ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ርሳቸውስ ይህን ይላሉ?

ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል የተባሉት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሌ ብለው በጋዜጦች ባሰራጩትና የመጨረሻ ቃላቸውን በሰጡበት ጽሁፍ ‹ሰኔ 11/1999 ኣም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካኝነት መንግሥትንና ሕዝብን ይቅርታ ጠያቄአለሁ፤ይህ ብፈልግም ልለውጠው የማልችለው ሀቅ ነው› በማለት በግልጽና በአደባባይ ይቅርታ መጠየቃቸውን አምነዋል አረጋግጠዋል፡፡ ታዲያ ከዚህ በኋላ እስርን ያውም ህግን ባልተከተለ ሁኔታ እንደ ወንበዴ ከመነገድ ይዞ ምን አመጣው፡፡ መልሱ ቀላል ድርጊቱ ግን ከባድ ነው፡

ወ/ት ብርቱካን የተናገሩት ያልሆነ ፈጥረው አይደለም ፤ቀድሞ ያልተነገረ አዲስ ነገርም አይደለም፡፡ ነገሩ ሳታመካኝ ብላኝ እንደሚባለው ነው፡፡ የይቅርታ ሂደቱና ማሳካታቸውን በገለጹት ሽማግሌዎች የተነገረ መንግስትም የተቀበለው አለያም ያልተቃወመው ነበር፡፡ ሀምሌ 13/1999 ማርፈጃው ላይ ይቅር ተባዮቹ የቃልቲን ወህኒ ቤት ከመልቀቃቸው ቀደም ብሎ የተሰራጨውና ተደጋግሞ በመገናኛ ብዙሀን የተደመጠው ‹ ከፕ/ር ኤፍሬምና ከሀገር ሽማግሉዎች የተሰጠ › ተብሎ ፕሮፌሰሩንና ቀሪዎቹን ሽማግሌዎች ሁለት የተለያዩ አካላት አድርጎ ገልጾ የወጣው መግለጫ ‹ ምርጫ 97 ተከትሎ በሀገራችን በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ችግሩ ሰላማዊ እልባት እንዲያገኝ በአገራዊ ወግ መሰረት መፍትሄ ለማፈላለግ ለ18 ወራት ያህል ጥረት ስናደርግ ቆይተናል ›በማለት የፈጀውን ግዜና ለውጤት የተበቃበትን መንገድ ይገልጻል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም በይቅርታ ጉዳይ በአዋጅ ስልጣን የተሰጣቸው የይቅርታ ቦርዱም ሆነ የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት እንዳልነበሩበትና ጉዳዩ ያለቀው በጠቅላይ ምኒስትሩና በታሳሪዎቹ መካከል በተደረገ የመልእክት ንግግርና በተደረሰ ስምምነት መሆኑን የሽማግሌዎቹ መግለጫ እንዲህ በማለት ያስረዳል፡፡‹ ለክቡር ጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ አመራር ቅንነትና አርቆ አስተዋይነት በአድናቆትና በትህትና እናመሰግናለን› ካለ በኋላ ትንሽ መስመሮችን አልፎ ‹እስረኞቹም የቀረበውን ሀሳብ ተቀብለው የምህረት ጥያቄው እንዲሳካ በማድረግ ጥረታችን ውጤታማ ይሆን ዘንድ ለሰጡን በጎ ምላሽና ላሳዩን ክብር በፈጣሪ ስም እናመሰግናለን› ይላል መግለጫው፡፡ በህግና በህግ ብቻ ይቅርታ የተሰጠው ወገን እንኳ ደስ ያለህ ይባላል እንጂ በምንና ስለምን ይመሰገናል፡፡ የጠየቀ ሲመለስለት የለመነ ሲያገኝ አመስጋኝ እንጂ ተመስጋኝ አይሆንም፡፡ ተደራድሮ ሲሳካ ሁለቱም ወገን ትንሽ ትንሽ ከፍላጎቱ ትቶ ለይቅር ለእግዚአብሄር ሲንበረከክ ያኔ ሁለቱም ወገን ይመሰገናል፡፡ በሽማግዎቹ አማካኝነት የሆነው በፍጻሜው ሽማግሌዎቹ የተናገሩትም ይህን ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን ቃሌ ብለው ባሰነበቡን ጽሁፋቸው የገለጹትም ይህን ሀቅ መሰረት ያደረገ ነው: እውነት ቢፈራና ህግ ቢከበር ቃላቸውን ያፈረሱት ጠቅላይ ምኒስትሩ ናቸው፡፡ ያን ግዜ ከጭንቀት ለመገላገል የፈጸሙትን በሽማግሌዎቹ ሲነገር አምነው የተቀበሉትን ዛሬ በሁለት እግራቸው

ሲቆሙ ወይንም የጎን ውጋቶች ሲያስ ቸግሯዋቸው ካዱት፡፡ ፈሪሀ እግዚአብሄር ቢኖርና ሊላው ቀርቶ ለህሊና ተጠያቂ መሆን ቢቻል ለነገሩ እዚህ መድረስ ምክንያቶቹ ሽማግሌዎቹ ናቸው፤ ሰራን ብለው የፎከሩበትንና ሽልማት እስከመቀበል የደረሱበትን በወቅቱም በአደባባይ በኩራትና በድፍረት ሲናገሩት የነበረውን ጉዳይ ዛሬ የአቶ መለስን ፊት አይተው መደበቃቸው በሰማይም በምድርም ይቅርታ የማይገኝለት ለዘመናት ያካበቱትን መልካም ስም( እኔ አላውቅም ካላቸው ማለቴ ነው) ጨርሶ የሚንድ ነው፡፡ የፖለቲከኞቹ ይህን ሀቅ በድፍረት መናገር ያለመቻል በተለይ ደግሞ የአንድነት አመራር ከጅምሩ እስካሁን የፈተጸመውና የቀጠለበት ክህደት የመነግስት ባላስልጣኖች ስህተታቸውን መለስ ብለው ከማየት ይልቅ ልክ ነን ብለው እንዲገፉበት ያስቻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ወ/ት ብርቱካን ለእስር የተዳረጉበትን ምክንያት በዝርዝርና በድፍረት የጻፉ እዚህ ሀገር ውስጥ እኔ የማውቀው አንድ ሰው ናቸው ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ፡፡በዚህ አድራጎታቸውም የህሊናቸው ጌታ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡ የወገኖቻቸውንም አክብሮት አግኝተዋል፡፡
( በነገራችን ላይ እኚህ ሰው በሁለተኛው ጽሁፋቸው የብርቱካን እስር ተገቢና ህጋዊ ነው ሲሉ የነበሩትን በመነግስት ሰፈር የሚኖሩትን አቶ ጌታቸው ረዳን ዳግም ብእር እንዳይነሱ ያደረጉ ሰው ናቸው)

‹ብርቱካንን መንገድ በመንሳት ወይንስ ይቅርታ በማንሳት› በሚል ርዕስ በአዲስ ነገር ጋዜጣ መጋቢት 12/2001 ዓም ባስነበቡን ሁለተኛ ጽሁፋቸው ‹ በእኔ እምነት መንግስት ወ/ት ብርቱካን የተቀበለችውን ይቅርታ አለማንሳቷን መቀበል ያልፈለገበት ምክንያት በሽምግልና ከተገኘ ይቅርታ ይልቅ በህግ ሂደት ለተገኘ ይቅርታ ይበልጥ ክብደት ስለሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በሙግት ላይ ያለ አንድሰው ጉዳዩ በህግ አለቀልኝ ሲል እና በሽምግልና አለቀለኝ ሲል ያለው ትርጉም የተለያየ ነው፤በሕግ አለቀልኝ ሲል የሕጉ መንገድ ፍጹማዊ እና ብቸኛ ድል ማገኘቱን የሚያሳይ ሲሆን በሽምግልና አለቀልኝ ሲል ደግሞ በድርድር በውይይትና በመቻቻል ብያኔውን ማግኘቱና ያሳያል፤ መንግስትም በሽምግልና የተገኘውን ይቅርታ ትቶ ብቸኛና ፍጹማዊ ድል ያጎናጽፈኛል ብሎ የሚያምንበትን በህግ ሂደት የተገኘ ይቅርታ የሚመርጥ በመሆኑ ወ/ት ብርቱካን የተቀበለችውን ይቅርታ ያለማንሳቷን ማረጋገጫ ቃል አልተቀበለም› ብለዋል፡፡ እውነታው ይህ ነው፡፡ መንግስት የፈለገው ደግሞ ያልተፈጸመውን ነው፡፡ ያልሆነውን፡፡ በህግና በህግ ብቻ ነው ይቅርታ የተሰጠው ሽምግልና ብሉ ነገር አልነበረም ብሎ ለመከራከር ቀርቶ ለመናገር ግን የሚደፈር ያለ አይመስለኝም፡፡ ከላይ በመግቢዬያ ላይ የገለጽኩትን አዲስ ዘመን ያስነበበንን ሽምግልና አልነበረም አሉ የተባለውንም ጠቅላ ምኒስትሩ ዳግመኛ ስለመናገራቸው አላውቅም፡፡

ይቅርታው የተከናወነው በሽምግልና መሆኑን ማሳየት ብቻ አይደለም በሚገባ ከሚያረጋግጡት ከዚህ በላይ ከተነሱት ጉዳዮች በተጨማሪ የይቅርታ ሥነ ሥርዓት አዋጅ 395/96 በመጠቀስ መከራከር ይቻላል፡፡ ውጤት የሚገኘው ግን ማንም ሰው ከህግ በላይ አይደልም የሚለው የህግ መርህ ጠቅላይ ምኒስትሩም ቢሆኑ፤ ፕሬዝዳንቱም ቢሆኑ፤ንጉሱም ቢሆኑ፤የመከላከያ የደህንነትን የፖሊስ ባለስልጣናትም ቢሆኑ ተብሎ ገቢራዊ ሲሆን ነው፡፡ በእኛ ሀገር ይህ አይታይም፡፡ ሌላውን ብንተወው በዚህ ጽሁፍ የተገለጹት የፖሊስ ባለሥልጣናት ወ/ት ብርቱካንን ሲጠሩና ሲያስፈራሩ ከህግ በላይ ሆነው ነው፡፡ ታህሳስ 20/ 2001 ዓም ይቅርታውን ሰርዞ ወ/ት ብርቱካንን ወደ እስር ቤት መላኩን በይፋ በድፍረት በመግለጫ የነገረን የፍትህ ምኒስቴር መስሪያ ቤት ያንን ለማድረግ የሚያ ስችለው አንዳችም የህግ መሰረት አልነበረውምና ራሱን ከህግ በላይ አድርጎ ነው፡፡ ለዚህም ነው የወ/ት ብርቱካን ህገ ወጥ እስር የአንዲት ወጣት ሴት እስር ብቻ ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን የህግ የበላይነት መከበር ጥያቄም የሚነሳበት፡፡ ዓለምም የጮኸበትና የጮኸለት፡፡ በሽምግልና የተፈጸመን ነገር፤ይህንኑም በወቅቱ አምኖ ተቀብሎ ሌሎች ሲናገሩትም ማሳሰር ቀርቶ ያላስጠየቀን ጉዳይ የፈሩትን ሰው ከመድረኩ ለማስወገድ ምክንያት አድርጎ ማቅረብ ‹ህግ በጦር መሳሪያ መሀከል ሲሆን ዲዳ ነው› የሚለውን አባባል የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የይቅርታ አዋጁ፤

1. አንቀጽ 14 ይቅርታ የሚጠየቀው የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ ነው ይላል፡፡ 18 ወራት የፈጀ የተባለውን ሂደት ትተን ራሱ መንግስት የነገረን የይቅርታ ደብዳቤ ላይ ታሳሪዎቹ የፈረሙት ሰኔ 15/1991 ዓም ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ፍርድ የሰጠው ደግሞ በራሱ በመንግስት እንደተገለጸው እኛም በፍርድ ቤት ተገኝተን እንደተከታተልነው ሀምሌ 9/1999 ዓም ነው፡፡ ይህም የይቅርታ ጉዳዩ ከፍርድ በፊት ማለቁን ያረጋግጣል፡፡

2. አንቀጽ 4(1) የይቅርታ ጥያቄውን በመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለፕሬዝዳንቱ የማቅረብ ስልጣን የይቅርታ ቦርዱ መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ጠቅላይ ምኒስትሩ የታሳሪዎቹን የይቅርታ ደብዳቤ ለቦርዱ ማስተላለፋቸው የተገለጸው ሀምሌ 9/1999 ዓም ፍርድ ቤቱ በአብዛኛዎቹ ተከሳሾች ላይ የእድሜ ልክ እስራት መፍረዱን የገለጸውን ዜና ተከትሎ በዛኑ እለት ነው፡፡ እስረኞቹ ቃሊቲን የለቀቁት ደግሞ ሀምሌ 13/1999 ዓም፡፡ ይህም የይቅርታው ሂደት ያለቀው አስቀድሞ ስለመሆኑ ይመስክራል፡

3. የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግስት በአንቀጽ 71(7) በህግ መሰረት ይቅርታ ያደርጋል በማለት የቅርታ የመስጠትን ስልጣን በብቸኝነት የሰጠው ለፕሬዝዳንቱ ነው፡፡

ፕሬዝዳንቱ ይህን ተግባር የሚፈጽሙት ደግሞ የይቅርታ ቦርዱ በአዋጁ በተገለጸው አግባብ አጣርቶ ሲያቀርብላቸውና ርሳቸውም ሲያምኑበት ነው፡፡ ደብዳቤው ከጠቅላይ ምኒስትሩ ወደ ቦርዱ ሀምሌ 10 ደርሶ( ምክንያቱም ሀምሌ 9 ችሎቱ ሲነሳ የሥራ ሰኣት አልፎ ነበርና ነው) ቦርዱ አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረቡን ስራ፤ ፕሬዝዳንቱም የራሳቸውን የማጣራት ተግባር በሶስት ቀን ውስጥ አጠናቀው ነው ይቅርታው የተሰጠውና እስረኞቹ ሀምሌ 13/1999 ለመፈታት የበቁት ብሎ ለመቀበል ቀርቶ ለመናገር ይቸግርል፡፡

ጉዳዩ በሽምግልና መከናወኑን ብቻ አይደለም ሂደቱም ሆነ ፍጻሜው ከህግ ይልቅ ፖለቲካዊ እንደነበረ ህጋዊ ለማስመሰል የተከናወኑ የማስመሰል ስራዎች ራሳቸው ይመሰክራሉ፤

ከላይ እነደተገለጸው ጠቅላይ ምኒስትሩ በእስረኞቹ የተፈረመውን ደብዳቤ ለይቅርታ ቡርድ የላኩት ሀምሌ 9 የመጨረሻው ፍርድ ከተሰጠ በኂላ ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ በፊት ፓርላማ ላይ በህግ የተያዘ ጉዳይ ላይ ሽምግልና እንዴት ይካሄዳል በሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ከኢህአዴግ ነበር፡፡ ይህ ሆን ተብሉ እንዲነሳ የተደረገም ይሁን ጠቅላይ ምኒስትሩ ችግሩን ለመፍታት የሄዱበትን መንገድ በመቃወም የቀረበ ርሳቸው የሰጡት መልስ ግን በአሳሪና ታሳሪ መካከል ድርድር ሊካሄድ እንደማይችል፤ የይቅርታ ጥያቄ ግን እንዳለና ይህም ሊስተናገድ የሚችለው ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ በኂላ እንደሆነ፤መንግስታቸው በፍርድ ቤት ስራ ጣልቃ እንደማይገባ በመግለጽ ነበር፡፡ በወቅቱ የመንግስት ዋና ፍላጉት እስረኞቹን የሚፈታበት የወንድ በር ማግኘትና በተለይ ለሚሊኒየሙ አከባበር የፖለቲካውን አየር ማረጋጋት ሲሆን በታሳሪዎቹ በቤተሰቦቻቸውና በህዝቡ ዘንድ ደግሞ የእስረኞቹ ለቤታቸው መብቃት ስለነበረ ብዙ ያልተነሱ ጥያቄዎች ነበሩ ፡፡ለወ/ት ብርቱካን እስር ምክንያት የሁነው ጉዳይም በወቅቱ ከላይ ከተገለጸው ፍላጎት አንጻር በሁለቱም ወገን ተለባብሶ የታለፈ መሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ጉዳዩ ለእስር ካበቃ ያኔ የተተዉ ጥያቄዎችን ማንሳት ግድ ይሆናል፡፡ መንግስት በፍርድ ቤት ጣልቃ ካልገባ፤ ይቅርታው የታየውም ከፍርድ በኂላ ጠቅላይ ምኒስትሩ ደብዳቤውን ሀምሌ 10/1999 ኣም ለቦርዱ ከላኩት በኂላ ከሆነ የፍትህ ምኒስትር ባለሥልጣኖች ቦርዱን ወክለው ደብዳቤው ላይ የሰፈረው ፊርማ የእስረኞቹ መሆኑን ለማረጋገጥ ቃሊቲ መገኘታቸውን ከፍርዱ በፊት የሰማነው እንዴት ሆኖ ነው፡፡ ጠቅላይ ምኒስትሩ የይቅርታ ደብዳቤውን ለቦርዱ መላካቸውን የገለጸው ዜና ቢያንስ ይህን አላገናዘበም፡፡

ቃሊቲ ተገኝተን እያንዳንዱን እስረኛ አነጋግረን የራሱ ፊርማ መሆኑን አረጋግጠናል ካሉት አንዱ የፍትህ ምኒስትር የነበሩት ናቸውና ይቅርታ የሚጠየቀው ከመጨረሻ ፍርድ በኂላ መሆኑንና የይቅርታ ደብዳቤ ሊያዛቸው ይገባል ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 13 ከተዘረዘሩት 13 ነጥቦች አንዱንም እንኳን ያልያዘ መሆኑን እያወቁ ፖለቲካዊውንና በሽምግልና ወደ ፍጻሜ

የተቃረበውን ጉዳ ህጋዊ ካባ ለማላበስ ሲሉ ብቻ ግልጽ የሆነ የህግ ጥሰት መፈጸም ከርሳቸው የሚጠበቅ አልነበረም: ነገሩ የሕግ ሳይሆን የጉልበት ሆነ እንጂ፡፡ ይህም ሆኖ ግን ጉዳዩን በህግ የተፈጸመ ይቅርታ ሊያሰኘው አይበቃም፡፡

ሂደቱን መለስ ብሎ ላጤነው የድብብቆሽ ጨዋታውን በግልጽ ማየት ይችላል፡፡ መንግስት ጉዳ ዩን በሽምግልና ጨርሶ ነገር ግን ህጋዊ ካባ በማላበስ በህግና በህግ ብቻ የተጠናቀቀ ነው ማለት ይፈልጋል፡ ይህም ከላይ በገለጽነው ዶ/ር ዳኛቸው ባነሱት መሰረታዊ ጭብጥ ላይ ይመሰረታል፡፡ ይህን በደንብ ለማስመሰል እንዳይቻል ደግሞ ታሳሪዎቹ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ካወቁ በኋላ አቶ መለስ በፈለጉት ሁኔታ ደብዳቤውን እንደማይፈርሙ ከ18 ወራቱ ሂደት ታይቷል፡፡ ስለሆነም ክሱ ይቋረጣል፤እናንተ ከፈረማችሁ ፍርድ ቤት ብሎ ነገር አይኖርም በማለት እንዲፈርሙ ተደረገ፤ የፍትህ ምኒስቴር ሰዎችም ቃሊቲ ሄደው በማነጋገር የማስመሰያ ስራ ሰሩ: ከዚህ በኋላ ጉዳዩ ወደ ኋላ ተመለሰና የፍርዱ ሂደት ቀጠለ፤ሲፈረድም ደብዳቤው ወደ ቦርዱ ተላከ ተባለ፡፡ የድብብቆሽ ጨዋታው  ወደ ኋላ የተመለሰበት አካሄድ ድርጊቱ እንዳይታወቅ ማድረግ የሚያስችል አልነበ ረም፡፡ ይልቁንም የራሳቸው ንግግር ዜናና መግለጫ ጨዋታውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ እንጂ፡፡ ተከራካሪ ሰውም ለክርክር የሚሆን የህግ መድረክም ያለመኖሩ እንጂ ቃልን በማጠፍና ስምምነትን በማፍረስ የመጀመሪያው ተጠያቂ አቶ መለስ ዜናዊ ሁለተኛው ደግሞ ፕ/ር ኤፍሬም ይስሀቅ በሆኑ ነበር፡፡

ስለ ብርቱካን ህገ ወጥ እስር ሲነሳ የመንግስት ወገኖች እንዳይነሳባቸው ስለሚፈልጉ ሌሎቹ ደግሞ ስለሚፈሩ እያዘለሉት እንጂ ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ይህ ነው፡፡ ይቅርታው የተሰጠው በሽምግልና ነው ወይንስ በህግና በህግ ብቻ፡፡ ወ/ት ብርቱካን ያለአግባብ ታስረው ይህ አልበቃ ብሎ ህክምና እንዳይገኙ፤ መጽሀፍ እንዳያነቡ፤ራዲዮ እንዳያዳምጡ ከሰው እንዳይገናኙ፤ በወዳጅ ዘመድ እንዳይጠየቁ ተከልክለው ህገ ወጥ ብቻ ሳይሆን ኢ-ሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ይህን ሀቅ ለመናገር ብሎም ለመከራከር ያለመድፈር የራስ ወዳድነታችን የደረሰበትን ደረጃና የፍርሀታችንን መጠን ነው የሚያሳየው፡፡ በተለይ የሽማግሌ ተብየዎቹ ነገር ያሳዝናል ብቻ ሳይሆን ያሳፍራል፡፡ ለነገሩ ሰሚ ጠፍቶ እንጂ ገና ሽምግልናው እንደተጀመረ ፕ/ር አለማየሁ ገብረማርያም በስፖርተኛና በጡረተኛ ፕ/ር የፖለቲካ ጉዳይ ሊሸመገል እንደማይችል እንደማይ ገባም ተናግረው ነበር፡፡ ሽማግሌ በቃሉ የሚጸና በቆመበት አድሮ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡